# የጠቅላይ ሚኒስትሩ የእውቀት ሌብነት (plagiarism ) ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ያለው መልዕክት፣

ከዶ/ር አገሬ አበበ

ሰዎች አማራ ስልሆኑ ብቻ እንደ አውሬ እየተጨፈጨፉ ነው። ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ተፈናቃይ በአማራ ክልል ውስጥ ይገኛል። የኑሮው ውድነት ጣራ ነክቶል። ዜጎች በሰላም ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አልቻሉም። አገራችን በብዙ በከፋ መከራ ላይ ናት። አሁን ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እዉቀት ሌብነት ለምን መጨነቅ አስፈለገ የምትሉ አንደምትኖሩ እገነዘባለሁ። ምንም እንኳ የህዝቡ መከራ በመቀጠሉ ቅድሚያ ትኩረት ቢያሻም፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተደጋጋሚ የእውቀት ሌብነት (plagiarism) በቀላሉ ሊታለፍ አይገባም። ምክንያቱም ለአገርና ለትውልድ አደጋ ስለሆነ ነው።

የመቶ ሃያ ሚሊዮን ህዝብና የጥንታዊቷ አገራችን ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር ያልሆኑትን ሆኖ ለመቅረብ፣ ያላወቁትን አዋቂ ሆነው ለመታየት፣ ራሳቸውን ከሁሉ በላይ፣ የሁሉም ነገር አዋቂ አድርገው ማየታቸው አደጋው በቀላሉ መታየት የለበትም። ከሸመደዱትና የራሳቸው አስመስለው ካቀረቡ ከሄነሪ ኪሲንጀር ንግግር፣ ከቀድሞው ፕሬዘደንት አባማ ንግግር ጀምሮ ሚኒስትሮቻቸውን በሚይሰለጥኑባቸው አቅርቦቶች እና፣ ምንም እንኳ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚሰራ የወያኔ የውጭ ክንፍ ቢያወጣውም፣ በዶክትሬት መመረቂያቸው የምርምር ጽሁፍም ግልጽ የእውቀት ስርቆት /plagiarism/ ፈጽመዋል። ሚኒስትሮቻቸውን ባሰለጥኑበት አቅርቦት የራሳቸው አስመስለው ለስራው ባለቤት እውቅና ሳይሰጡ ያቀረቡት ስዕልና ሃሳብ ከሌላ ሰው ሥራ የተገለበጠና የተበረዘ ነው። ለዚህም ተገቢው ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል።

ጠ/ሚ አቢይ በኩራት እንደራሳቸው ስራ አድርገው ያቀርቡትና ሚንስትሮቻቸው በትጋት ኖት ሲይዙ፤









https://www.youtube.com/watch?v=Edks6t5FD7Q

የሚከተሉት ስዕሎች በስራቸው ካለው ድረገጽ ላይ የሚገኙና ምናልባትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እውቅና ሳይሰጡ መረጃውን የገለበጡባቸው ምንጮች ናቸው።




https://www.pinterest.com/pin/comparison-between-transformative-and-informative-learning-methods--59391288809008624/




http://factmyth.com/the-left-right-political-spectrum-explained/




https://directionlessbones.wordpress.com/2009/09/04/the-political-compass-and-class-politics-a-better-wa-to-classify-ideologies/

አመራር /leadership/ ማለት ራዕይ በጋራ ነድፎ፣ ባለሙያዎችን ለይቶ በተገቢው ስራ በመመደብ፣ ባለሙያዎችን ለስራ አነሳስቶና አበረታትቶ እውቅና ሰጥቶ፣ የሰራተኞቹን እውቀትና ክህሎታቸውን በተገቢው ቦታና ጊዜ ተጠቅሞ ወደታለመው ግብ ወይንም ራዕይ መድረስ ነው። መምራት ወይም መሪነት ማለት የሁሉ ነገር በሁሉም ዘርፍ አዋቂ መሆን አይደለም። መምራት አዋቂዎችን አሰባስቦ አቅጣጫ ማስየት እንጂ። ሁሉን አዋቂ ሰው የለም። ሁሉን ነገር አዋቂ መስሎ መገኘትና ትህትና ማጣት የአላዋቂነት መለያ ነው። ሌላው ሰው ያመነጨውን እውቀት ለባለቤቱ እውቅና ሰጥቶ መጠቀም ከአንድ አገር መሪና የዶክትሬት ድግሪ አለኝ ከሚል ሰው ቀርቶ ከማንም ጤነኛ ሰው ይጠበቃል። እውቅና ሰጥቶ መጠቀም ደካማ አያስብልም። ስህተትም አይደለም።

አሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገሪቱን ወደ አዘቅት እየወሰዷት ያለው እርሳቸው ስለራሳቸው እውቀት ያላቸው የተሳሳተና ከገደብ በላይ የገዘፈ አመለካከት ነው። ይህም ከሌሎች ምክርና ሃሳብ እንዳይቀበሉ አድርጓቸዋል። በዚህም ሰጥ ለጥ ብለው የሚገዟቸውና ምንም ጥያቄ የማይጠይቋቸውን፣ አስተያየት የማይሰጧቸውን፣ የጎሳ ወኪል ነን የሚሉ ደካሞችን እየመረጡ ወደስልጣን ይመድባሉ። ብዙዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወጣት ስለሆኑ ነው፣ ቀስ በቀስ ይማራሉ፣ ይታረማሉ፣ በማለት ታግሰዋቸው ቆይተዋል። ዶ/ር አቢይ ግን በትዕቢት ላይ ትዕቢት፣ በአላዋቂነት ላይ ሌላ አላዋቂነት፣ በእውቀት ሌብነት ላይ ሌላ የእውቀት ሌብነት እየጨመሩ ነው። የጠ/ሚ አቢይ ገበና ቢሸፈንላቸው ይሻላል ተብሎ ብዙ ሰው ዝም ብሎ ቆይቷል። አሁን ግን ሊማሩ ባለመቻላቸውና አገርን ከጥፋት ለማዳን ሲባል በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል።

ደርግ ብዙ አዋቂዎችንና ልምድ ያላቸውን በፖለቲካ እምነታቸው ብቻ ገድሏል። መለስ ዜናዊ አገር መምራት የጀመረው የተሻሉ ያውቃሉና ልምድ አላቸው የተባሉትን  ሁሉ ከመንግስት ስራና ሃላፊነት በማባረር ነው። በጎሳ ፖለቲካ  ታውሮ፣ ሲቪል ሰርቪስ “ኮሌጅ” የሚባል የካድሬ ማሰልጠኛ በመክፈት፣ ቢሮክራሲውን ከሲቪል ሰርቪስ ዲግሪ በተቸራቸው ደካሞች በመሙላት አገርን ጎድቷል። እውቀት ሁሉ ከኢሃዲግና ከመለስ ዜናዊ እንደሚመነጭ ታመነ። ታዋቂ የተባሉትን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን ሳይቀር ከስራ አባረረ። መለስ ዜናው በስህተት የሚናገረው ቃል የአነጋገር ዘየ ሳይቀር በቀቀን በሆኑት የኢህአዲግ ካድሪዎች ተጠንቶ እንዳለ ይደገም ነበር። አሁንም በጠ/ሚ አቢይ ጊዜ ይህ ልምድ ተጠናክሮ ቀጥሏል። እነዚሁ ከሲቪል ሰርቪስ “ኮሌጅ” ድግሪ የተቸራቸው ሰዎች አሁንም የአገርቱን ስልጣን ተቆጣጥረዋል።

ጠ/ሚ አቢይ ከ 15 አመታቸው ጀምሮ በዛው ስርዓት ተኮትኩተውና ስርዓቱን በታማኝነት እያገለገሉ ከፍተኛ ስልጣን ይዘው አድገዋል። ብዙዎች ተዓምራዊ ነገር ጠብቀው እንጂ፣ ጠ/ሚ አቢይ የኢሃዲግን የጎሳ አፓርታያድ ፖለቲካ እንደጡጦ እየጠቡ አድገው፣ የተለየ ሃሳብ ይዘው ሊመጡ አይችሉም። ቁጥር 2 ኢህአዲግም ከቁጥር 1 ኢህአዲግ የሚለየው ህወሃት በኦሆዲድ/ ኦሮሞ ብልጽግና/ መተካቱና በአማራው ላይ የከፋ ጭፍጨፋና ማፈናቀል ማድረጉ ነው። አሁን ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ፣ ለኢሃዲግ ቁጥር 2 ካድሪዎችና ሚኒስትሮች፣ ሌሎች ምሁራን የደከሙበትን እውቀት፣ እውቅና ሳይሰጡ፣ እንዳለ እየገለበጡና እየቦጨቁ፣ የራሳቸው አስመስለው፣ በማቅረብ (የእውቀት ሌብነት/plagiarism/ በመፈጸም “አዋቂነታቸውን” ለማሳየት እየሞከሩ ነው።

ይህ ደግሞ በብዙ መንገድ አገር ይጎዳል። እውቀትና አዋቂዎችን ከመግፋታቸው በተጨማሪ፣ ለወጣቱ ትውልድና በትምህርቱና ምርምር ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች መጥፎ አርዓያ እየሆኑ ነው። ወጣቱ ትውልድ የሰው ስራን /እውቀትን/ መስረቅ ትልቅ ስራ ከማስያዝ አልፎ የአገር መሪ ያደርጋል የሚል የተሳሳተ አመለካከት እንዲፈጠርበት ያደርጋል። አገራችንንም በአለም ፊት ያዋርዳል።  የሰው ስራን ለእውቀቱ ባለቤት እውቅና ሳይሰጡ እንደራስ ስራ አድርጎ ማቅረብ ለአገር አይጠቅምም። እንዳውም የበታችነትና ጥገኝነት ስሜት ይፈጥራል። ከሁሉም በላይ ለእውቀትና ትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተተኪ ትውልድ ያሳጣናል።

ምንም እንኳ በኢሃዲግ ቁጥር 2 ካድሬዎች እየተመራ ቢሆንም፣ ለጠ/ሚ አቢይ የዶክትሬት ድግሪ የሰጣቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ  በዶክትሬት መመረቂያቸው የምርምር ጽሁፍ የፈጸሙትን የእውቀት ስርቆት /plagiarism/ በአግባቡ መርምሮ ተገቢውን እርምጃ መውሰድና ለህዝብ ማሳወቅ አለበት። ይህ ካልሆነ ዩኒቨርሲቲው በአለም አቀፍ ደረጃ በአካዳሚኩ ማህበረሰብ የተወገዘ ይሆናል። ከዩኒቨርሲቲውም የሚመረቁ ተማሪዎች በውጭ ኒኒቨርሲቲዎች እውቅና እንዳያገኙ ያደርጋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ  አካዳሚክ ሴኔት በዚህ ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰብ ተገቢ ነው።